

# ኢትዮጵያ

ኅዳር ፳፻፭ | ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፩ | በነፃ የሚሠራጭ

## አበራሽ በርታ

## መምህር በላይነህ ገ/ማርያም

### በሞቱ ጠላቶቹን ድል የነሳ የኢሕአፓ ኮከብ

(ምንጭ፤ ጎሕ መጽሔት ሚያዝያና ግንቦት ፲፱፻፺፫ ዓ.ም)

ገፅ ፯

**ሀገር ከፋሺስትም ከጠባብ ይበልጣል!**

**ተዋርዶ ከመኖር መሞት ይመረጣል!**

**በዘር ከመራራቅ አንድነት ይሻላል!**

**ከድርጅት አጥር ነፃነት ይጠብቃል!**

**አንገት አጎንብሶ ግፍን ከማራዘም፤**

**ደንታ ቢስ ከመሆን ለወገናችን ደም፤**

**ጥርት ባለው መስመር ለትግል እንትመም!!!!!!!**

## ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች የሰላማዊ ትግልን ምንነት እያሳዩ ነው::

ልክ አምና በዚህ ወር ጀምረው አይበገሬ ወገኖቻችን ሀይማኖታቸውን መሠረት አድርገው የኢትዮጵያዊነት ማንነታቸውን በትግል እያሳዩ ነው።

የኢትዮጵያውያን ሙሲሊሞች የመብት ትግል የሕዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይን ሥርዐት ልኩን እያሳየው ነው:: ላለፉት 21 ዓመታት ዘረኝነትን የመጫወቻ ካርድ ሕዝቡ ሲጫረሥ ከቦ ለመሞቅና ሥልጣኑን ለማራዘም ያሰበው ሰይጣናዊ ተንኮል አወሊያዎች ራሱ ላይ እንዲፈነዳ አድርገውት የፈንጂው እሳት ራሱን የወያኔን ሥርዓት እያነደደው መሆኑን ይኸው የአንድ ዓመት ጉዞአቸው ለአለም አሳይቷል። አኸምዱሊላሂ፤ እግዚአብሔር ይመስገን። ከአወሊያ ተቋም ተለኩሶ ወደአንዋር መስኪድ አቅንቶ በየኢዱ በካምቦለጆ ሚሊዮኖች እየወጡ ሰላማዊ ሕዝባዊ ትግል ምን



በማድረግ ሀገራችንን በቁም ሲገሸልጥና ሲግጥ የከረመው ወያኔ ለቀጣይ ሃያ ዓመት ያቆየኛል ብሎ ያቀደው ዋንኛው አኩይ ሴራ በኢትዮጵያውያን ሙሥሊምና ክርስቲያን መካከል ፈንጂ ቀብሮ አንድ ቀን በማፈንዳት እንደሆነ ሃያ አንድ ዓመታት በሰላም ትግል ስም ለሚያሾፉ "ምሁር የተቃዋሚ መሪዎች" ትልቅ ትምህርትን ሰጥቷል። የሚማር ከተገኘ ማለት ነው።

ወደ ገፅ ፯ ዞሯል

## መምህር የኔሰው ገብሬ ተከበረ



ስም ከመቃብር በላይ ይውላል ይባላልና

አምና ይህን ግዜ የወያኔ ሥርዐት እንደቁስል ሲጠዘጥዘው ስርአቱን ተጠይፎ ራሱን በራሱ ቤንዚን አርከፍክፎ መባእ የሆነውን የኔሰው ገብሬን ለመዘከር በእለተሰንበት በደብረሃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስትያን (2601 Everts street NE, Washington DC 20018) በደማቁ ተወድሷል፤ ታሪኩ ተነግሯል፤ ተገጥሞለታል፤ ሻማም ተበርቶለታል። በደቡብ ኢትዮጵያ መምህር የነበረው ወጣቱ የኔሰው ገብሬ በገዛ ሀገሩ ባእድ በማእዱም ቀላዋጭ መሆን ዘግንኖት ኢትዮጵይ ጥቂቶች አንገቷን አንቀዋት ከሥርዋ ሲወዘውዝዋት ቆሞ መመልከት ያልሆነለት ጉብል ኅዝባዊውን ትግል በገላው ላይ በለኮሰው እሳት የማይጠፋ ዘላለማዊ የነጻነት ችቦ አቀጣጥሎ የገዛ ክቡር ኅይወቱን ለክብርት አገሩ አይከፍሉ መሥዋትነት የከፈለ በርእግጥ ሁል ጊዜ መከበር አለበት።

የዛሬ ፴፰ ዓመት የጓዶቹንና የድርጅቱን ገበና ላለማጋለጥ ራሱን ከፎቅ ወርውሮ የሰዋውን የኢሕአፓውን ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ በጽናቱና በቆራጥነቱ ታሪኩን የሚጋሩና የሚያውቁ ራሱን አሳልፎ ስለምስጠቱ ሲናገሩ ተረት ይምስል የነበረውን ያህል እነሆ ዛሬም አምባገነን በኀለበተበት ሥርአት ራሱን ጧፍ አድራጊ ይፈጠራልና እነሆ በዘመነ ወያኔም እንደየኔሰው ገብሬ ራሱን ሳይሆን የሥርአቱን እድፍ በገላው ነዲድ አሳይቷል::

ወደ ገፅ ፪ የዞረ






# ኢትዮጵያ

**በኢሕአፓ የዲሲና አካባቢው ደጋፊ አካል**

**የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ**



አድራሻ 5309 Georgia Ave. NW. 2nd fl. Washington DC 20011
ስ/ቁ 202 291 4217
ኢሜል dc.region.eprp@gmail.com


## ርዕሰ አንቀጽ
## ምሁራን ሆይ ወዴት ናችሁ?!

አገርና ወገን በዕወቀት ከተለቁ ልጆቹ ብዙ የሚጠብቅ መሆኑ ተደጋግሞ ተነግሯል። መደጋገሙ ግን ሰሚዉን ያሰለች እንደሆን እንጂ እዉነትነቱን ከቶ አያደበዝዘዉም። ሳይማር ያስተማረ ሕዝብና ዕዉቀትንና ክብርን ያጎናጸፈች ደሃ ሀገር የዉለታ ምላሽ ቢጠብቁ አበዛችሁት አይባሉም። ምሁሩም በበኩሉ ትምሕርት ባነጸዉ የአዕምሮ ባለቤትነቱ፤ የሰዎችን ነጻነትና አስተሳሰብ የማራመድን ማህበረሰባዊና ግላዊ ኃላፊነት በጫንቃዉ የተሸከመ መሆኑ እሙን ነዉ ።

የሕዝባዊነቱ መመዘኛም ይህንኑ ተልዕኮዉን በብቃት ከመወጣቱ አንጻር የሚሰላ ነዉ ። ታሪክ እንደሚያመለክተዉ ፤ ኢትዮጵያዊነት አደጋ ላይ በወደቀባቸዉ የአርበኛነት ዓመታትም ሆነ ብዙሃኑ ዜጎች መብትና ክብራቸዉን በተገፈፉባቸዉ አገዛዞችና ማኅበራዊ ሥርዓቶች ዉስጥ ምሁራኑ ኢትዮጵያዉያን በተደጋጋሚ አላባ ከገለባ ተለይተዉ ተሰፍረዋል። በትዉፊታዊዉም ሆነ በዘመናዊዉ ትምህርት የተፈሩትን ጨምሮ፤ ተጎንባሾቹና ለጥቅማቸዉ ያደሩቱ ፤ አንድም በወራሪነት ባህር አቋርጦ ከመጣዉ ጠላት ጋር ተሰልፈዉ ኢትዮጵያን ወግተዋል። አንድም ባለጊዜ በነበሩቱ አገዛዞች ስር ተሰልፈዉ የተገዢ ወገኖቻችንን ዘመነ ፍዳ አራዝመዋል። በአፋራሹ ደግሞ ሕዝቡን የወገኑቱ በመከራና ሥቃይ እሳት ተጠብሰዉ፤ ለተሰለፉበት ዓላማና እዉነት በጽናት እየዘመሩ በጀግንነት ተሰዉተዋል። በመዋል በማደር ፤ ከሃድያኑ ሀፍረትንና ዉርደትን ሲከናነቡ፤ የኋለኞቹ አይበገሬዎች ግና መጪዉ ትዉልድ ሁሉ በኩራት አንገቱን የሚያቀናበትን አንጸባራቂ የተጋድሎ ታሪክ አስመዝግበዉ አልፈዋል።

ታሪክ ራሱን መድገሙ ስመረለት መሰል፤ ዛሬም ኢትዮጵያዊነት በከፍተኛ ፈተና ዉስጥ በወደቀበት ጊዜ ላይ እንገኛለን። ሕዝብ በለየለት ዘረኛ አምባገነናዊ ሥርዓት ዉስጥ በጭቆና ሰንሰለት እግር ተወርች ተኮድኩዶ የመከራን እንቆቆ እየተጋተ ነዉ። የዜጎች ፈቃድ የተገፋበት፤ ድምጻቸዉ የታፈነበት፤ ፍትህ የተነፈገበት፤ በሰላም ወጥቶ መግባታቸዉን ብቻ ሳይሆን የዕለት ምግባቸዉን ሳይቀር አይተማመኑበት፤ የቀቢጸ ተስፋ ዘመን ከባተ ሁለት አሥርት ዓመታት ተቆጥረዋል። በኢትዮጵያ ሕዝብና በወያኔ አገዛዝ መሃከል ያለዉ ቅራኔ የማይታረቅ ደረጃ ላይ ደርሷል ።

በዚህ እዉነታ ዉስጥ፤ ዘረኛዉን አገዛዝ ለጥቅም ሲሉ ከተወዳጁት ወገኖች ዉጭ ያለዉ የሀገሪቱ ምሁር እጆቹን አጣምሮ ሁኔታዉን በአርምሞ የሚከታተል ባዕድ ታዛቢ መስሎ ይታያል። ያለዉ ሥርዓት በትግል መወገድ ያለበት መሆኑን ቢገነዘብም እንኳ ለሚያስከፍለዉ ዋጋ ዝግጁ አይደለም። በሌሎች መሥዋዕት ዉጤት ነጻነቱን ለመቀዳጀት የሚቋምጥ፤ ወይም ፈረሰኛዉን ዉሃ ደፍሮ በዋና በማቋረጥ ፈንታ ዉሃ ሙላቱን ለማባበል ማሲንቆዉን መገዝገዝን የመረጠዉን አዝማሪ ይመስላል ።

ይህን መሰሉ አቋም የትም አያደርስም ። እንደ ሰጎን አንገትን አሸዋ ዉስጥ በመቅበር በገሃድ ከሚስተዋለዉ ትንቅንቅም ሆነ ከህሊና ሙግት መሰወር አይቻልም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተማሩት ልጆቹ ብዙ ይጠብቃል። ጎራ ለይቶ የተያያዘዉን ፀረ-ወያኔ ትግል እንዲመሩለት፤ ካልሆነም እንዲያግዙለት ይጣራል። አለን ማለት የወግ ነዉ፤ "ምሑራን ሆይ..ወዴት ናችሁ?"

ሕዝባዊዉ ዴሞክራስያዊ ትግል ያቸንፋል!
ኢትዮጵያ በነጻነቷ ኮርታ ለዘለአለም ትኑር!

## የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች

በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኙ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች በየሁለት ሳምንቱ የሚያካሂዱትን መደበኛ ስብሰባ ባለፈው እሁድ በደማቅ ሁኔታ አጠናቀዋል። በወር ሁለት ጊዜ የሚገናኘው ይኸው ስብስብ በርካታ ደጋፊዎቹን በማሳተፍ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ሰፊ ውይይት አድርጓል። በዚሁ ስብሰባ በተለይ ወያኔ እያካሄደ ያለውን በልማት ስም ኢትዮጵያን የማፈራረስ ታሪኳንም የመበረዝና የመደለዝ እኩይ ተግባር ለመግታትና ለመከላከል የበኩሉን የዜግነት ድርሻ ለመወጣትና የፓርቲውን መመርያ በቁርጠኝነት ተግባራዊ ለማድረግ እንደወትሮው ሙሉ ስምምነት ላይ ደርሶል።

በተጨማሪም ፀረ ውያኔው ሁለንተናዊ ትግል ይጠነክር ዘንድ የሕዝበ ሙስሊሙን ሕዝባዊ ትግል ከበርካታ ግፍና በደል የወለዳቸው የሕዝብ አመጾች ጋር በማቀናጀት በተግባርና በተጨባጭ ለማገዝ በሙሉ ስምምምነት ፕሮግራሙን ከረጅም ሰዓታት ውይይት በኋላ አጠናቆ በቀጣዩ መደበኛ ስብሰባ ለመገናኘት ቀን ወስኖ ተለያይቶል።

## የኔ ሰው ገብሬ ተከበረ

ከ ገፅ ፩ የዞረ

በእለተ እሁድ ሙት ዓመቱ ነበር እና ጀግናውን ያደነቁ ሀገር ወዳዶች ተሰባበው የምስዋትነቱን አንደኛ አመት አከብረዋል። በእለቱ ታሪኩ የተነበበ ሲሆን በወጣቶቹም በግጥም ታስቧል። ከእንግዶቹ አንዱ የነበሩትም አርበኛው አባት አቡነ ፊሊጶስ ከሰማእቱ ዝክር አስከትለው ከህዝቡ አብራክ ተከፍለው የኢትዮጵያውያንን እሮሮ በማባባስ ላይ ላሉ የወያኔ ቅልብ ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳዮች የመዘዛችሁትን ስለት ከህዝባችሁ ወደአምባገነኑ ታዞሩ ዘንድ ሲሉ በተለይ ለጦሩ አባላት የቀጥታ ጥሪ አትርበዋል።
ክብር ሞቱ ለሰማዕቱ!!
የኔሰው ገብሬ የኛ ነው!!

በእለቱ በወጣቶች ከቀረቡት ግጥሞች

## የኔ ሰው የኛ!!

በኛነት መከራቱ ታሪክ መዘከሩ፤
ኢትዮጵያዊ ሆኖ በሐገር መከበሩ፤
በሰንደቅ አላማ በአንድነት መኖሩ፤
ምኑ ያስቀይማል ምንድንው ችግሩ?

ፍትህ ልማት ስንል የለም እትከፋፍሉን፤
ነፃንትን ስንል በዘር አትለያዩን፤
ዴሞክራሲ ባልን እንቢኝ አትግደሉን!
ሰብአዊ መብት ስንል እንቢኝ አትውገሩን!

እንቢኝ እንቢኝ እንቢኝ በግፍ አንገዛም!
መጋዝ መሰደዱ አይበቃም አልበዛም!?
እንቢኝ ኢታፍኑን!
እንቢኝ አትለያዩን!
ኢትዮጵያም ጀግና አላት
እራሱን አቃጥሎ ቤዛ የሚሆናት!

መታሰር መጋዙ የቁም ሞት መሞቱ
ረሃብ ጥማቱ ስቃይ እንግልቱ
እያደረ ቢብስ እጅጉን ቢጠና
በወያኔ ብረት ጦብያ ታፍና
እስከመቼ ግዞት ወዲያልኝ አለና

እምቢኝ እሻፈረኝ አላቸው የኔ ሠው
ትግሉን ኢጋግሞ እሳቱን ለኮሰው!
ዛሬም እንደትላንት ኢትዮጵያ ጀግና አላት
እራሱን አቃጥሎ ቤዛ የሚሆናት!

እንዶጧፍ ነዶ ሲቃጠል እያየው
የገብሬን አንበሳ ሞቷል የሚል ማነው?

እንደጓድ አበራሽ ታስራም ሳትረሳ
ሀገሬን የምትል ተነስ እንንሳ!
ወገኔን የምትይ ተነሽ እንነሳ

መከፋፈል ይቅር እንቁም አንድ ላይ
ወገን ተሰቃይቶ ሲቃጠል እንዳናይ
ተረግጦ መገዛት መጋዝ መሰደዱ
በጣምራ ከንዳችን ከሃገር ይውገዱ
የኔ ሰው የኛ ነው ከቶ አይዝልም ከንዱ

ዛሬም እንድትላንት ኢትዮጵያ ጀግና አላት
እራሱን አቃጥሎ ቤዛ የሚሆናት
እራሱን አቃጥሎ ቤዛ የሚሆናት !


**ለስራ ፈላጊዎች:**

የ **HESS** ጋዝ ማደያ ገንዘብ ተቀባይ ይፈልጋል።
አድራሻ: **9142 Richmond hwy**
**Fort Belovir ,22060**
**Phone: (202) 415-1764**

## የወያኔ ባለስልጣናት መተራመሳቸውን እንድቀጠሉ ነው

እርስ በርስ ባለመተማመን እየታመሱ የሚገኙት የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት ከመቼውም ጊዜ በላይ ግራ ተጋብተው በየቀኑ በድንገተኛ አስቸኳይ ስብሰባ ተወጥረው እንደሚገኙ ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሏል:: እርስ በርስ እየተሻኮቱ የሚገኙት የወያኔ ባለስልጣናት አንዱን ሲቋጥሩ ሌላው እየተፈታባቸው ውለው ጠዋት የወሰኑትን እንደገና ከሰአት በሁዋላ እየሻሩ ባለበት በአሁኑ ወቅት "እራሳችንን እናጽዳ" የሚል አዲስ ዘመቻ መጀመራቸውም ታውቋል::

ቅዳሜ ጥቅምት 24 ቀን 2005 ዓ.ም የወያኔ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ድንገተኛና አስቸኳይ ስብሰባ አደረገ የተባለ ቢሆንም ስለዋሉበት ስብሰባ እንዳችም ነገር ሳይገለጽ በመቆየቱ የመካከለኛውና የታችኛው ካድሬ በጉዳዩ ግራ ተጋብቶ ሲታመስ እንደነበረም የደረሰን ጥቆማ አስረድቷል:: አስቸኳይ የወያኔ ስራ አስፈጻሚ ስብሰባ ከመደረጉ አስቀድሞ በነበሩት ቀናት ውስጥ በተከታታይ "እራሳችንን እናጽዳ" በሚል በፓርላማ ህንጻ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ በዝግ ሲነታረኩና ሲወዛገቡ የሰነበቱ መሆኑን የጠቆሙት እነዚሁ ውስጥ አዋቂ የድርጅቱ አባሎች የንትርኩን ሂደት ለህዝብ በመገናኛ ብዙሀኖች እንደወረደ ይፋ እንዲደረግ ብለው ውሳኔ የተላለፈና ማስታወቂያ የተነገረ ቢሆንም በማግስቱ የተባለው ቀርቶ ሊታፈን እንደቻለም እነዚሁ ምንጮች አረጋግጠዋል::

የወያኔ ቡድን ሰሞኑን በአራት ኪሎ በሚገኘው በፓርላማው የቋሚ ኮሚቴው መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ባልተለመደና እስከዛሬ ባልታየ ሁኔታ እርስ በርስ ሂስ እና ግለሂስ መሰል ኑዛዜ ሲያደርጉ ከመሰንበታቸውም በተጨማሪ የውይይቱ መንፈስና ውሳኔ በመገናኛ ብዙሀን ይፋ ይደረግ ተብሎ ውሳኔ ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም በበረከት ስምኦንና በጥቂት የህወሀት ሰዎች ሳንሱር ተደርጎ ከቀናት በሁዋላ መቅረቡን ተከትሎ በወያኔ ቡድን ውስጥ ችግር መኖሩን የሚያሳይ ነው ሲል የእነዚሁ ውስጥ አዋቂ የድርጅቱ አባላት ጥቆማ አብራርቷል::

ማዕከላዊነት እየተዳከመና በአጭር ጊዜ ውስጥ የወያኔ ቡድን ሊሰነጠቅ ይችላል ተብሎ ከፍተኛ ስጋት ውስጥ በወደቀበት በዚህ ጊዜ ዝግ ስብሰባና ንትርክ ባደረጉበት ወቅት ከፍተኛና ነባር የወያኔ ባለስልጣናት ከወጣቶች አፍለኛ ባለስልጣናት ጋር በሀሳብ ልዩነት ፈጥረው እርስ በርስ ሲነታረኩ የሰነበቱ ሲሆን በተለይ የህወሀቱ አባይ ጸሐዬ እስከ ዛሬ በህዝብ እና በሀገር ላይ ሲፈጽሙ የነበረውን አዳፋ ታሪክ ለመደበቅ እና ከተጠያቂነት ለማምለጥ በድፍኑ ሸፋፍኖ ለማለፍ ሙከራ ሲደረግ የነበረ ቢሆንም ወጣቶቹ የነበረውን የተሳሳተ አሰራር በግልጽ እያስቀመጡ ሲተቿቸው እንደነበር ከምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሏል::

የነባር በረሀ አመጣሽ ባለስልጣናት እና አፍለኛ ወጣት ባለስልጣናትን ለማግባባት መሀል ሰፋሪ ሆኖ ሲያንቀሳቅስ የነበረው ምርኮኛው የአሀዴዱ አባዱላ ገመዳ፣ ስራቸውን በአግባቡ የማይሰሩ…

ወደ ገፅ ፯ የዞረ

## ዜና ክተባለ

ስዩም መስፍን ወይም በቀድሞ ስሙ ስዩም ሙሳ ወደ ቻይና በአዜብ መስፍንና በረከት ሴራ ከመላኩ በፊትም በድንገት ከስቶና ሞግጎ ብዙዎችን ያቺ እነ ባጫ ደበሌና ጀኔራል አበባየሁን የያዘች ዘመናዊ በሽታ ያዘችው እንዴ አስብላ ነበር ። ዛሬ ዕድሜ ለሳይንስ በህክምና ሃይል ከሞት መዳን መሰንበት ተችሏልና ስዩምን ወደ ባንኮክና አሜሪካ የወሰድው ኤይድስም በአዜብ ብስጭትም አይደለም ። እሱን እንኳን ይዞት ይሂድና ዶክተር መረራ ደግሞ ምን ነክቶት ከሳ? ዶክተሩ ከመኢሶን እስከ ኦብኮ ፖለቲካዊ ጉዞአችው ባያምርም ቧልተኛ ናችውና ቢከርሙልን ቢያንስ ያስቁናል። "ትግል ከድራፍቴ ጋር" ያሉትን ያስታውሷል። የወያኔ ቁንጮዎች ከታመሙ ከሁለት አስርተ ዓመታት በላይ ቢያስቆጥሩም ዘንድሮ ጠንቶባችዋል። ስዩም፣ በረከት፣ ተፈራ ዋልዋ፣ ኩማ ደመቅሳ ወዘተ ሁሉም ገመምተኛ ናችው። አንዳንድ ተራቢዎች መለስን በሞት ሊያጅቡትና ታማኝነታችውን ሊያረጋግጡ ቸኩለው ነው ይላሉ። ኣያረጉትም አይባልም። ባረገው! መልከኛው ኮሶ ቢጠጣ ጭሰኛውን አስቀመጠው ይባል አልነበር። ለእኛ ሊያሳስበን የሚገባው የራሳችን በሽታ ነው፣ ድክመታችን ።

ከወደ ጀርመን አንድ የመረረው ዜጋ አንድ ኮማንዶ በሚል ርዕስ ሽንጎ ሽግግር ካውንስል ትብብር ጥምረት ወዘተ በሚል የተሰባሰቡትን ዘርዝሮ አቅርቦልናል። አልቻልንም አቅም የለንም ኣስግድሎ ባያውቅም በነዚህ ስብስቦች የሚገኙት አብዛኞቹ ዛሮች ቢጠፉ ቁጥቋጦች ተሰለፉ ናችው። ተሰለፍ ተደርደር ተቆጠር ቢባሉ በአቃቂ ፋብሪካ ሁለት ጣቱ የተቆረጠ ላባደርን ጣቶች ቁጥር አይበልጡም። ሳይከካ ተቦካ ነውናም ገና ሳይገዘፉ፣ ተዋግተው መሬት ነፃ ሳያወጡና ገገርውን ከፍል በትግል ሳያስጨንቁ ዓለም ወያኔን ወግድ ብሎ እውቅና ይስጠን ብለው መሳቂያም አድርገውናል። ይባስ ብለውም ወደ ዩጋንዳ የተላከው እገሌ ነው ብለው በይፋ በማዉጣት ግለሰቡን ለወያኔ ጥቃት (ንቆ ካልተወው ) አጋልጠዋል። በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ ተብሎ የለ? ይህን የተዘበራቀቀ ሁኔታ ማስወገድ ካልተቻለ ወያኔ ይመቻቻል ገና ለብዙ ዓመታት ። ሌሎች ደግሞ በቀጣይ አልሰሜኑት መወዝወዙን መርጠው የአስመራው ፍለጠው ቁረጠው ኢትዮጵያን ለማዳን ይረዳናል ብለው ወደዚያ መጓዙን መርጠዋል። ምርጫ ማድረግ መብታችው ሲሆን መታለልና ገደል መንከባለል ደግሞ ሀገርን ጎጂ ነው።

የዓይጥ ምስክሩ ድንቢጥ እንዲሉ የመኢሶን ሁለት የቆዩ መሪዎች መለስ በመሞቱ የሚመጣ የወያኔ መታመስ የለም፤ የወያኔ መዋቅር የረጋና የተጠናከረ ነው ቢሉም ወያኔ በውስጡ በከፍተኛ ደረጃ በመታመሱ የተነሳ የዓለም አቀፍ ስምምነቶችንም መፈረም አቅቶት እንዳለ ነጮቹ እየዘገቡ ናቸው። አንዳንድ ወያኔዎች ራሳቸው እንደሚሉት ከሆነ ደግሞ ክፍፍሉ ወደ ስራዊቱ እየዘለቀ ነውና ቀውሱ መጥፎ ውጤት ይኖረዋል። ሚዳቋዋ ወያኔ አሁን ያጋጠማትን የመከራ ጉድጓድ ዘላ በቀላሉ የምታመልጠው አይመስልም። እንዳታመልጥም ማድረግ የሀገር ወዳዱ ዜጋ ግዳጅ ነው ። ወያኔ ውስጣዊ ቅራኔዋን በውጭ ጦርነት ልትወጣ ትጥር ይሆናልም ተብሏል። ይህ ኤርትራን የመውረር ዕቅድ በነ በረከት የሚደገፍ አይደለም። ሌላ የልዩነት ነጥብ። የተሐድሶ ግድብ የተባለውን ( ዛሬ የመለስ ግድብ እንበለው ባይ አድርባዮች አሉ) በተመለከተም ልዩነት ተከስቷል "አያስፈልግም፤ ግልገል ጊበ 3 ከተጠናቀቀ ይልቅስ የተከዜን ግድብ እናድስ" ባዮች አሉ።

ወደ ገፅ ፬ የዞረ

## ምን ይሰማ…አገር?



*"…እንደሚታወቀዉ በሙስሊሙና በኢሕአዴግ መሃከል የነበረዉ ግንኙነት እኛ እስከምናዉቀዉ ድረስ እስካለፈዉ ዓመት ድረስ በጣም ጥሩ የሚባል ነበር፤……."
(የኢሳቱ ፋሲል የኔዓለም የኢትዮጵያዉያን ሙስሊሞችን እንቅስቃሴ በተመለከተ ከአቶ አብዩ ያሲን ጋር ያደረገዉን ቃለ ምልልስ የከፈተበት መደምደሚያ (ኢሳት ቴቪ -ትኩረት ኖቬምበር ፳፻፲፪ ))

- ይኼ ሥልጡን ጋዜጤኛነት ፤" ልማታዊ ልማታዊ " መሸተት ጀመረሳ ።…ወይስ እናንተ የምታዉቁት እዉነት ከድፍን አገር ዕዉቀት ጋር ይጣረሳል?…አንዋር መስጂዶች / ገና ለታመመዉ "የሕዝብ ዐይንና ጆሮ" ሕክምና ተጨማሪ ትግል ይጠብቃችኋል።

* "ወ/ሮ አዜብ የባለቤታቸዉን ምስጢር ይፋ አደረጉ፤"
(ጎልጉል ድረ-ገጽ ኖቬምበር ፲ ቀን ፳፻፲፪ ያሰፈረዉ ዜና ርዕስ።)

- ምነዉ ፤ ምነዉ ፤የአዋጁን በጆሮ? ምስጢርነቱማ ካከተመ ዘመናት ተቆጠሩ። ጋዜጠኛዉ ተፈራ አስማረ አገሩን ለቅቆ የተሰደደዉ "ትግራይ እስከትለማ -ሌላዉ አገር ይድማ" ብሎ ባስነበበ መስሎን ።

* "ከማስተር ፕላን ዉጪ ቤታችን ፈረሰብን ያሉ የዓለም ባንክ አካባቢ ነዋሪዎች ፍትህ እየጠየቁ ነዉ።"
(ሪፖርተር ጋዜጣ ፤ ኅዳር ፲፩ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም እንዳሰፈረዉ፤)

- የትኛዉን ፍትህ ነዉ የሚጠይቁት ፤ ለመሆኑ ፍትህ ባገር አለ እንዴ? …" ዳኛዉ ከፊት ሲሸሽ ሕጉ ሲያባርር ፤ ሁሉም ተያይዘዉ ጠፉ አሉ ካገር " ተብሎ ከተገጠመ ቆየ እኮ።

* "Ethiopia discussing war with Eritrea ."
(ኢንዲያን ኦሺን ኒዉስሌተር ፤ኖቬምበር ፲፯ ቀን ፳፻፲፪ እንደዘገበዉ:)

- ምነዉ ፤ ስብሃት ነጋ ሞተ እንዴ ? …..እንዴት አልሰሞተንም በሉ?/

*ሕዝቡ ከማጉረምረም አልፎ ንዴቱን በእንቅስቃሴ ለማሳዬት ዝግጁ የሆነ አይመስልም፤"
(ሪፖርተር ፤ ሕዳር ፲፱ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን ጠቅሶ እንደዘገበዉ)

-"አይመስልም?"..ርስዎም እርግጠኛ አይመስሉም ዶክተር

* "በደል ይረሳል ፤ ወይስ ይለመዳል ?"
(ይኸ ነዉ አንተሁነኝ ፤ኖቬምበር ፳፯ ቀን በኢትዮ ፎረም ድረ ገጽ መጣጥፋቸዉን ያስነበቡበት ርዕስ)

- በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሁለቱም መልስ ነዉ።

ከገጽ ፫ የዞረ

ከገንቢው የጣሊያኑ ሳሊኒ ጉቦኣችውን ውጠውና በሕዝብም ላይ በሚካሄደው ዝርፊያ ሊከብሩ የተነሱት ደግሞ ግድቡ ካልተሰራ በሚል ኡኡ እያሉ ናቸው። ለነገሩ ግድቡ ከሶስት ዓመት በኋላ ያልቃል የተባለው ውሸት ነው። ለማንኛውም በወያኔ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስር የተቋቋመ የሕዝብ የዲፕሎማሲ ተቋም የተባለው ወደ ግብጽ ተጉዞ ግብጾቹን ግድቡ ቢሰራም አይጎዳችሁም ብሎ ሊያሳምን ይጥራል ተብሏል። የዚህ የወያኔ መሳሪያ ተቋም አባላት በአብዛኛው የትግራይ ተወላጆች ናቸው። የሪፖርተሩ አማረ አረጋዊ፤ የማነ ብርሃን፤ ዶክተር ብርሃኔ ገብሬይ፤ የሚጠቀሱ ናችው። በአድርባይነት ደግሞ ሜዳሊያ አይስጥም እንጂ እንደነ ፕሮፌሰር ላፒሶ ዓይነት አድር ባዮች በዚህ በወያኔ ኮሚቴ ገብተው አስየው በተባሉ ነበር። በአባይ ጉዳይ በኢትዮጵያና ግብጽ መሃል ያለው ቅራኔ ቀልድ ሳይሆን የሀገርን የነገ ዕጣ የሚመለከት ነው። ኢትዮጵያ ካንቀላፋች ግብጽ ትጠቀማለች.። የተሕድሶ ግድብ ተብየው ሕዝብን ምዝርፊያ ነው እንጂ ፍሬ አልባ መሆኑ አከራካሪ ኣይ.ደለም። ምኞች ግን ከገንዘባቸው መለያየትን እስከፈለጉ ድረስ ማቆም አይቻልም። ነገ የህዝብ ቀን ሲመጣ ይጠየቁበታል.። ዋ ያቺ ጊዜ ስትመጣ!

ከዚህ ከዚያ ስንል ደግሞ ዜና ከተባለ ተጨማሪ ነገሮች አሉ። ወያኔዎች እርስ በርስ ተናከሰው ዓለም አቀፍ ሰነዶችን ሳይቀር መፈረም አቅቷችዋል። ውስጣዊ ቅራኔዎች ግለዋል። ይህ ከፍፍልም ወደ ሰራዊታችውም ወርዶ አደጋ ላይ ጥሏቸዋል። ስብሐት ከሳሞራ ታርቆ በረከትና አዜብን እያጠቃም ነው ተብሏል። ቅራኔው ውሎ አድሮ ወደ መፈንቅለ መንግስት ሊያመራም ይችላል እየተባለ ነው። ያርገው! ያባላቸው! በሕዝብ ደረጃ በሙስሊም. ኢትዮጵያውያን የሚደረገው ትግል በቀሪው ሕዝብ እየተደገፈ ነውና ውጤቱ ገንቢ መሆኑ የሚታወቅ ነው። የወያኔ ቀብር ቀን እየደረሰ ነው። ህጋዊ የተባሉት ተቃዋሚ ሀይሎች መንግስት ኣላነቃንቅ አለን በሚል ሽፋን ቆሞ መሞትን መርጠዋል። ሙስሊም ወገኖች የወያኔን ፍቃድ ሳይጠይቁ እያካሄዱት ያለው ተቃውሞ እንኳን ትምህርት ሊሆናቸው አልቻልም። ችግሩ ወኔን የሚመለከት ነው። የተቃውሞ ትግል የሚካሄደው በአገዛዙ ፍቃድ አይደለም፤ አገዛዙን ተቃውሞ እንጂ። ለነ በየነ ጴጥሮስ ማን ይህን ነግሮ! ግማሾቹም ተማሪ ሆነናል ብለው ባዕድ ሀገር ናቸው። ይባስ ብለውም ታላቅ ሰው ሞተ ብለው ለሀገር ጠላት ሊያለቅሱም ዳድቷቸው ነበር። ሌሎች ደግሞ ከተመከሮ

አልማር ብለው ለኢትዮጵያ ጥፋት የታገለው ሀይል ዛሬ በተዓምር ለኢትዮጵያ ነጻነት ይቆማል ብለው ወደ አስምራ እየተጓዙ የሚድከሙ አሉ። የአግዓዚ ሀላፊ ሆኖ በ 1997 ፍጅት ተጠያቂ የሆነው ኮልኔል አለበል የግንቦት 7 ቡድን አባልና የመፈንቅለ መንግስት ሞካሪ ነህ ተብዬ ልያዝ ነበር ብሎ ወደ ኤርትራ ኮብልሎ በዚያም የአርበኞች ግንባር አባል ነኝ ብሎ ሳያድር በሻዕቢያ ትዕዛዝ ደግሞ የአማራ እንቅስቃሴ መሪ ነኝ ብሎ ተሰየመ። ዛሬ ደግሞ ኮሎኔሉ ወደ ስዊድን ሄዶ ጥገኝነት ጠይቋል። ላለፉት 20 ዓመታት ከሻዕቢያ ጋር ለማበር የሞከሩ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ደከሙ ተከፋፈሉ እንጂ ሲጠናከሩ ኣላየንም። አነግ ተባለ አርበኞች ግንባር ሁሉም. ተከፋፍለውና ታፍነውም ተሽመድምደዋል። ለወያኔ ሻዕቢያ ረድቶታል፣ ወያኔም የሻዕቢያን. ተቃዋሚዎች በማሽመድመድ አመሰግናለሁ ብሎታል። ወደ ሻዕቢያ እየነጎዱ ርዳን አግዘን ባዮቹ ይህ ነው የሚባል እርዳታ እንዳላገኙ የሚታወቅ ነው። ታዲያ ሌላ መፍትሔ መፈለጉ፤ በራስ ሀይል መተማመኑ ፤ መተባበሩ አይሻልም ነበር? ለዚህ ምክር ኣድማጭ ገና የለም ።

የሚከተሉትን ዜናዎች እስቲ እናጢናቸው ፤

• የወያኔ መንጋ ከቁንጮው ሞት በኋላ እንደተራበ ጅብ የሀገሪቷን ገንዘብ እየዘረፉ በመሆናቸው የውጭ ምንዛሪ እጥረት በጣም ከፍ ብሏል ተብሏል ።

• በደቡብ ኢትዮጵያ በተለይም በይርጋዓለም አማራ የተባሉት ከመንግስት መስሪያ ቤቶች ውዘተ እየተወገዱ መሆናችውንና አዋሳ ከተማ ራሷ ዳግማዊ መቀሌ ልትባል (ከትግራይ ተወላጆች ብዛት) ትንሽ ቀራትም እየተባለ ነው ።

• የሱዳኑን መሪ ለመገልበጥ የምዕራባውያን ሴራ እየተጧጧፈ ነው። በሱዳንና በደቡቡ ክፍል ዛሬም ቅራኔዎች የተባባሱ በመሆናችው ወደ ጁባ ንግድ ብለው የሚከንፉ ዜጎችም ኪሳራን ታቅፈው ይመለሳሉ እየተባለ ነው ።

• ስብሐት ነጋ አዜብ መስፍንን ከወያኔው ኤፈርት የንግድ ተቋም ሃላፊነቷ ለማስወገድ ሙሉ ጥረት ላይ ነውም ተብሏል።

• አዲሱ የግብጽ መንግስት በአባይ ጉዳይ ቋሚ የሀገሪቷን ፖለቲካ በመከተል ኢትዮጵያን የሚያምሱና የሚበጠብጡ ሀይሎችን ለማባበል እየጣረ ነው ተብሏል። እስካሁን አለን ብለው ካይሮ ድረስ የሄዱትን ሁሉ ግብጽ አትረቡም አትጠቅምኑም ሲል ዞር በሉ ብሏችዋልም ተብሏል።

የኬንያ ማሳዮች ሲተርቱ ሆድህ ርባና ቢስ እንዲያደርግህ አትፍቀድለት ይላሉ። አሜን !

መስተዋት ከድሬ

ኅዳር 22/2005

## ዓለም አቀፍ የኤይድስ ቀን

በመላው ዓለም ዛሬ ኅዳር 22 የሚከበረው የኤይድስ ቀን ይህ ቀሳፊ በሽታ በሀገራችን ላይ ያደረሰውን ከፍተኛ ጉዳት እንድንመረምር ያስገድደናል ። ያለው አገዛዝ የበሽታውን መጠን ሊደብቅ ቢጥርም፤ ካለፉት አመታት ሲተያይ የበሽተኛው ቁጥር ቀንሷል ቢባልም ብዙ ሚሊዮን ዜጎችን የሚያስቃይና ብዙ መቶ ሺዎችንም የገደለ መቅሰፍት መሆኑ የሚደበቅ አይደለም ። የ ኤይድስ ስርጭት ከነበረውና ካለው ሥርዓት ጋር የተገናኘም ነው ። ያለፈው አገዛዝ ኤይድስ ምንድነው ሲል ቢቃጣም አንድ ተከላካይ አቋም አቋቁሞ የመከላከል ጥረት ኣድርጎ ነበር። ይህን ተቋም ሳይውል ሳያድር ወያኔ ኣፍርሶታል ። በ ኤይድስ መከላከል ሽፋን አዜብ ጎላና ሚቿ አቡን ተብዬ ብዙ ሚሊዮን ዶላር ዘርፍዋል ። በ 1983 የወያኔ ወታደሮች በኤይድስ በስፋት ሲበከሉ ወያኔ እነዚህን በማከም ፈንታ ወደ ሌሎች ክልሎች መላኩና ጉዳት ለማድረስ መጣሩ የተጋነነ ወሬ ተብሎ የሚታለፍ አይደለም ። ኤይድስን በተመለከተ ሰፊ ቅስቅሳ ተደረገ ቢባልም በመሰረቱ ስርዓቱ በሀገር ደረጃ እያስፋፋ ያለው ጸያፍ ስርዓት ትልቁንም ወጣቱንም በሽታ ኣጋልጦታል ። የከተማው ቀርቶ በየገጠሩ ሚሊዩኖች የ ኤይድስ ሰለባ ሆነዋል ። የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣኖችና ጀኔራሎች የበሽታው ተጠቂዎች ናቸው ። ይህን ግን በይፋ አምነው አዲሱን ትውልድ በመምከር ፈንታ መደበቁን መርጠዋል ። ወያኔ የብልግና ስርዓትን እያስፋፋ ነውና ፤ ለባዕዳን ዝቅጠት ሀገሪቷን ከፍት አርጓልና ይህ የዘመኑ በሽታ ሊገደብ የሚችልበት ሰፊ ሁኔታ የለም ። ስለዚህም ዛሬ የ ኤይድስ በሽተኖች ቁጥር ቀነሰ ቢባልም ያለው በሽተኛ ቁጥር በጣም በጣም ብዙ ነው ።

አገዛዙ ብልሹ ነውና ያለው ሁኔታ ቀቢጸ ተስፋን የሚያስፋፋ ነው ። ብዙዎች መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ ለማድረግ ዝግጁ ኣይደሉም ። ወያኔ ታጋዩን የሀገር ወጣት ክፍል በተለይ ከጥቅም ውጪ ማድረግ ይፈልጋልና አልባሌ ልምዶች ወጣቱን እንዲበክሉ ይፈልጋል፡ ይጥራል ። ይህም ለ ኤይድስ ስርጭት እንዲሰራ ያደርገዋል ። ወያኔ በኢትዮጵያ ኤይድስ መሰራጨቱን --ከትግራይ ውጪ -- ይፈልገዋል ። በኤይድስ የተያዙትን የሰራዊቱ ኣባሎችን ለምን ከትግራይ ውጪ ኣሰማራ ታዲያ ? መሰል ብዙ ጥያቄዎች ኣሉ ። ዛሬ በዓለም ኣቀፍ ደረጃ የ ኤይድስ ቀን ሲከበር የ ኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ለዚህ ቀሳፊ በሽታ ዛሬም የተጋለጠ መሆኑን በማሳወቅ ነው ። ሀገራችን ለሀገር በቀልም ለባዕዳንም ባለጌዎች በወያኔ መተቃቧንም ማጋለጥ አለብን

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE

SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE

ድርጅትዎን በኢትዮጵያ

ጋዜጣ ያስተዋውቁ !

አድራሻ 5309 Georgia Ave. Nw , Washington DC 20011

ስ/ቁጥር 202 291 4217 e-mail: dc.region.eprp@gmail.com

# መምህር በላይነህ ገ/ማርያም

## በሞቱ ጠላቶቹን ድል የነሳ የኢሕአፓ ኮከብ

(ምንጭ፤ ጎሕ መጽሔት ሚያዝያና ግንቦት ፲፱፻፺፫ ዓ.ም)

በኛው የዘመን አቆጣጠር፤ አዲሱ የ፲፱፻፷፮ ዓመት መስከረም ላይ ሲጠባ ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማዋለድ ሲቀጣጠል የቆዬው ሕዝባዊ ትግል ቀደም ሲል የነበረውን ሰላማዊ ባህሪ ይዞ መቀጠል እንደማይችል ግልጽ ሆኖ ነበር። ፋሺስታዊው ደርግና ቅጥረኛ አገልጋዮቹ በሕዝቡ ዘንድ ያጡትን ተሰሚነት በኃይል ለመንጠቅ ታጥቀው የተነሱበት ወቅት ነበር። በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ላይ ሁለገብ ዘመቻ ተከፍቶበታል።የሕትመትና የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ብዙሃን ድርጅቱን የማጥላላት ተግባራቸውን አጠንክረው ገፍተውበታል። እልፎ ተርፎም፤ ኢሕአፓን ከሕዝቡ ልብ ባያስወጡት እንኳ፤ በድርጅት እንቅስቃሴው ረገድ ዳግም እንዳያንሰራራ አድርጎ ለመምታት ያስችላል የተባለ ዕቅድ ተነድፏል። ኢሕአፓን ነጥሎ ለመደምሰስ እንዲያመችም በድርጅቱና በአባላቱ ላይ "አናርኪስት" የሚል ታፔላ ተለጥፎባቸዋል። በሀገሪቱ ውስጥ በአራቱም ማዕዘናት ዉሎ አድሮ ሳያባራ ሊዘንብ ያቆበቆበውን የግፍና የፍጅት ዝናብ የሚጠቁም ዳመና ከአድማስ ላይ መታየት ጀምሮ ነበር ።

በዚህ ዕትማችን፤ አምዳችንን በተጋድሎው ብርሃን የሚያደምቅልን የኢሕአፓው ኮከብ መምህር በላይነህ በሕይወቱ ፍጻሜ ምዕራፍ ከሰው በላዎቹ የደርግ መርማሪዎች ጋር በተጋፈጠበት ቅጽበት በሰጠው ቃል የወቅቱን ሁኔታ እንደሚከተለው ገልጾት ነበር።

"የተካሄደብን የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ብቻ አልነበረም። አካላዊም ነው። የላባደሩ መሪዎች ከያሉበት ተለቅመው ታስረዋል። ወጣቶች ከየጉራንጉሩ ታድነው ለእስር ተዳርገዋል ። ታጋይ ሴቶችም እንዲሁ። ተራማጅ የገበሬ ማሕበራት መሪዎችና ገበሬዎች እስር አልቀረላቸውም።ደርግ ይህ ሁሉ አልበቃው ብሎ ሌላ ርምጃ ለመውሰድ መዘጋጀት ጀመረ። እንቅስቃሴውን ለመተግበርም ማናፋት ቀጠለ። ሬድዮና ጋዜጣው ሁሉ በርሱ ድንፋታ ተሞላ።...." በዚህም ሳቢያ ፤ ኢሕአፓ እስከዚያኔ ሲያራምደው የቆየውን ፤ ግለሰቦችን መግደል ለሕዝባዊው አብዮት ስኬት የሚፈይደው የለም በሚል አጽንዖት የሚደመድመውን መርሁን ቆም ብሎ እንዲያስብበት ተገደደ ። ምርጫው ሁለት ብቻ ነበር ። በወቅቱ የሕዝብ ጉዳይ ድርጅት ተብሎ ይታወቅ በነበረው ተቋም ውስጥ በተሰገሰጉ ባንዳ ካድሬዎች አጋፋሪነት ግዙፉን መንግሥታዊ የደህንነትና ወታደራዊ ኃይል በማሰለፍ ለተንቀሳቀሰው ፋሽስታዊ ድምሰሳ ቀላልና ምቹ ዒላማ መሆን፤ ወይም በአልሞት ባይ ተጋዳይነት የጠላትን ጥቃት መመከት። እርግጥ ነው ፤ሁለቱም አስቸጋሪ ምርጫዎች ነበሩ። ሆኖም በጊዜው በሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ለነበረውና በፈተና ሰዓት በማያፈገፍጉ ጠንካራ አባላቱ የጎለበተ ድርጅታዊ አቅም ለነበረው ኢሕአፓ እጅን አጣምሮ ትግሉን ከማስመታትና ሕዝባዊውን አብዮት በቀላሉ ከማስቀልበስ የሚከፋ ነገር አልነበረም። በመሆኑም የኃልያድን ያህል የገዘፈውን መንግሥታዊ ጥቃት የዳዊትን ቁርጠኛነት በተቀዳጀ ወኔና እልህ መጋፈጥ ብቸኛው አማራጭ ሆኖ ተገኘ። ፋሽስታዊው ደርግ ሰላማዊውን የትግል ዘዴ በማምከን የጀመረው ሽብር መስዋዕትነትንና አመፃን በአመፃ መጋተርን አስቸኳይ የመከላከያ ስልት ላደረገ ተግባር በር ከፈተ። በዚሁ መሠረትም መምህር በላይነህና ጓዶቹ ቁርጠኛና የማያወላዳ ርምጃ ለመውሰድ ተነሱ።

# ትላንትና



ቀዳሚው በትር የፋሽስታዊው ሥርዓት ቁንጮ በነበረው ጭራቅ፤ በሻለቃ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ላይ እንዲያርፍ ተወሰነ። ይህንኑ ውሳኔ በተግባር ላይ ለማዋልም አስፈላጊው ጥናትና መሰናዶ ከተደረገ በኋላ መስከረም ፲፫ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ዕቅዱ ሥራ ላይ የሚውልበት ዕለት እንዲሆን ተመረጠ።

## መስከረም ፲፫ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም፤

በዚህ ዕለት ለሚወሰደው ርምጃ አስፈላጊው ጥናት ተጠናቅቋል። ጥናቱ ሻለቃ መንግሥቱ በስንት ሰዓት ከሥራ እንደሚወጣ፤ በምን ዓይነት መኪና እንደሚሄድ፤ አጃቢዎቹ ምን ያህል እንደሆኑና በምን ያህል ርቀት እንደሚከተሉት፤ የሚሄድበት መንገድና አቅጣጫ የመሳሰሉት ጉዳዮች በዝርዝር ታውቀዋል። በዚሁ መሠረት ሻለቃው ከጽሕፈት ቤቱ ወጥቶ ጉዞ በሚጀምርበት ጊዜ ከደርግ ጽ/ቤት ግቢ ተከትሎት የሚወጣና ስውር ምልክት የሚሰጥ መኪና ተመደበ። ግቢውን ለቅቆ ከወጣ በኋላ በፖሊስ ጋራዥ ቁልቁል በመውረድ ወደ ራስ አበበ መንገድ ጉብቶ ከዚያም በጋንዲ ሆስፒታል አቋርጦ እንደሚሄድ በጥናት ተረጋግጧል። በመሆኑም የሰሌዳ ቁጥሩ 540 የሆነ አንድ ዳትሰን መኪና ፊቱን ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር አዙሮ ስታዲየም አጠገብ ከሚገኘው አጂፕ ቤንዚን ማደያ እንዲቆም ተደረገ። ጥቂት ፈንጠር ብሎ ደግሞ አንድ ፊያት 124 መኪና ከአንድ ዛፍ ስር እንዲቆም ተመደበ። በአፍሪካ ጎዳና ደግሞ አንዲት ቮክስዋገን መኪና የተመደበች ሲሆን በውስጧ ሆኖ ሁኔታውን የሚከታተል ሶስት ጓዶች የሚገኙበት አንድ ቡድን ተሰማርቷል። የቡድኑ አባላት ፤ መምህር በላይነህ ገ/ማርያም ፤ ግርማና ደምሴ ነበሩ።

በዕለቱ ሻለቃ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ከጽ/ቤቱ ወጥቶ ከተጠቀሰው ሥፍራ እንደደረሰ በመብራት ምልክት የሚሰጠው መኪና ግዴታውን ተወጣ። በዚሁ መነሽም ዛፍ ስር ቆማ ከነበረችው ታክሲ ተኩስ ተከፈተ። የታክሲዋን የተኩስ እሩምታ ለመርዳት የተመደበችው ዳትሰን መኪናም አከታትላ መተኮስ ጀመረች። ይሁንና በተፈጠረው ከፍተኛ ድንጋጤና ሽብር መሀከል ሞቱ የሚያርፍበትን ዒላማ የያዘው መኪና ሾፌር ሳያቆም ወደፊት ገሰገሰ። ዳትሰኗ ከኋላ እየተከተለች ሻለቃው ወደነበረበት ላንድሮቨር ጥይት ብታርከፈክፍም የተተኮሰው ጥይት በሙሉ የሚገባው በላንድሮቨሩ ሰውነት፤ በብረቱ ውስጥ ሆነ። ባላባራው የተኩስ ውርጅብኝ መሃከል ላንድሮቨሩ ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ በመግባቱ ዳትሰኗ ወደ ኋላዋ ዞራ ተመለሰች።

ታክሲዋም ቁልቁል ወደ ደብረዘይት መንገድ አቀናች። መምህር በላይነህንና ጓዶቹን የያዘችው ቮክስዋገን ከኋላ ሆና በመከተል ላይ ሳለች ተበታተኑ የሚል መልዕክት የሚያስተላልፍ ኃይለኛ የፍንዳታ ድምጽ በማስተጋባቱ ቁልቁል የቃሊቲን አቅጣጫ ተከትላ ተፈተለከች ። ሶስቱን ጓዶች የያዘው ቡድንም በቀጥታ ወደ መምህር በላይነህ መኖሪያ ቤት አመራ ።

## መምህር በላይነህ ገ/ማርያም -ሰዉዬው

በኛው አቆጣጠር በ፲፱፻፴፪ ዓ.ም ደብረ ብርሃን ከተማ ውስጥ ነበር የተወለደው ።ወላጅ አባቱ ለሥራ ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ በሄዱ በጥቂት ወራት ውስጥ ያሰቡት ስለተሳካላቸው ሕጻኑ በላይነህና ወላጅ እናቱም ለኑሮ ወደዚያው አቀኑ ። የቄስ ትምህርቱን በሩፋኤል ቤተክርስትያን ነበር የተከታተለው ።
በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም መድኃኔዓለም ት/ቤት ተመዝግቦ የአንደኛና የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቀቀ ።ለቀጣዩ ትምህርት አምቦ እርሻ ት/ቤት በመመደቡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እዚያው ተከታትሎ አጠናቅቋል።

በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም የአለማያን እርሻ ኮሌጅ የመግቢያ ፈተና በማለፉ ወደ ሐረርጌ አመራ ። በእርሻ ምህንድስና (አግሮ ኢንጂነሪንግ) የትምህርት ዘርፍ ተመድቦ ለሶስት ዓመታት ትምህርቱን ተከታትሏል ።ሆኖም ባጠቃላዩ የትምህርት ውጤት ተፈላጊውን ነጥብ ባለማምጣቱ ከኮሌጁ ተሰናብቶ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ ። በ፲፱፻፶ ዓ.ም ትምህርት ሚኒስቴር በመምህርነት ቀጠረውና በአዲስ አበባ ት/ቤቶች ጽ/ቤት ስብስቴ ነጋሲ ት/ቤት ተመድቦ አገልግሎት ጀመረ። የመነሻ ደመወዙም የኢት. ፫፻ ብር ነበር ።

መምህር በላይነህ በዚሁ ት/ቤት በማስተማር ላይ እያለ በ ፲፱፻፷፭ ዓ.ም (በአብዮቱ ዋዜማ) በአንድ የጥናት ክበብ ውስጥ በአባልነት ታቅፎ ጥናት ጀመረ ።የመለመለው የኢሕአፓ የወጣት ክንፍ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የነበረውና አለማየሁ ገ/እግዚአብሔር በሚል የምስጢር ስም የሚታወቀው አለማየሁ እግዜሩ ነበር ። የአዲስ አበባው በይነ ቀጠና አቃቂ ላይ የቀጠና ኮሚቴ እስካደራጀበት ሚያዝያ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ድረስ በጥናት ቡድን አባልነቱ ቆይቷል ። በዚህ ጊዜ ግን የኢሕአፓ ጊዜያዊ አባል ሆኖ ወደ አቃቂው በይነ ቀጠና በመዛወር ከሌሎች ጓዶች ጋር ሆኖ የመጀመሪያውን የፓርቲውን የቀጠና ኮሚቴ ለማደራጀት በቅቷል ።

የሚኖረው ቃሊቲ ውስጥ ላብ አደሮች በተበራከቱበት ሠፈር ውስጥ ነበር ።ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ሲነጻጸር የተሻለ ወርሐዊ ገቢ የነበረው ቢሆንም የበላይነህ ኑሮ ግን ከላብ አደሮቹ ያልተለየ ነበር ። በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ አልጋና ፍራሽ እንኳ እንዲኖረው ያልፈለገ ሲሆን ኬሻና ካሊም አንጥፎ ወለል ላይ ነበር የሚተኛው ። በአካባቢው ማሕበራዊ ሕይወት ውስጥ ግን ቀጥተኛ ተካፋይ ሆኖ ቆይቷል ። ጥብቅ የመጻህፍት ጓደኛ፤ ጸባየ ሠናይና እጅጉኑ ትሁህ ሰው በመሆኑ በሚያውቁት ሰዎች ሁሉ የሚወደሰው መምህር በላይነህ አሜሪካ ውስጥ ከሚገኝ አንድ ኮሌጅ ጋር በመጻጻፍ የሕግ ትምህርት ይከታተል ነበር። በዚሁ ጊዜም በቃሊቲ ወረዳ ሶሪቲ ከሚባለው ቀበሌ የገበሬ ማሕበር ውስጥ አንድ ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ተመርቶ ቤት ሠራ ።በዚያም አነስተኛ መጠን ያላቸውን የማስፈልፈያና የማሞቂያ መሣሪያዎች በመጠቀም የዶሮ እርባታ ጀመረ።

ወደ ገፅ ፯ የዞረ

# ማመጽ ክቡር ግዳጅ ነው!!

ነጋ ጠባ መሞኘት የሰውን ክብር ያጠፋል:: ልጅ ያሰኛል:: ጅልነቱ የሀገርን ዕጣ ፈንታ የሚመለከት ከሆነ ደግሞ ጉዳቱ ዜጎችንም ትውልድንም አስለቃሽ ይሆናል:: ወያኔ ስልጣን ይዞ ሀገር ሲያጠፋ ከሀያ ዓመት በላይ ሆኖታል:: የብዙሀንን ደም አፍሷል:: ሺዎችን ለስደት ለእስር ዳርጓል:: ሕዝብን ከጋምቤላ እስከ ኦጋዴን ጨፍጭፏል:: ከሁሉም የባሰ ወንጀሉ ደግሞ የሀገርን መሬት ለሱዳን አሳልፎ ሰጥቷል፤ ለም መሬቷን ለቻይና ለህንድና ለአረቦች አስረክቧል:: ወንጀል የከፋ የከረፋ ወንጀል:: ከሀደት ባንዳነት! ይህ ሁሉ እንዴት ይረሳል?

ወያኔዎች ፀረ ኢትዮጵያ ናቸው:: የድርጅታቸው መሰረታዊ መርህ ግብር ይህችን ታሪካዊ ሀገር ማዋረድ፤ ማንበርከክ ከተቻለም መበታተን ነው:: የስብሐት ነጋን ድንፋታ ያደምጧል:: የወያኔ ድርጅት ማገር ምሰሶው ኢትዮጵያን መጥላት ነው:: ትግላችን ፀረ አማራ ነው ሲሉ ያኔ ከምስረታቸው መልዕክታቸው ትግላችን ኢትዮጵያን ለማውደም ነው የሚል ነበር:: ይህን ደግሞ በተጨባጭ በተግባር አሳይተዋል፤ አስመስክረዋል:: የኢትዮጵያ ታሪክ መቶ ዓመት አይሞላም፤ የሀገር ታሪክ የሚባለው ተረት ተረት ነው ወዘተ እያለ ወያኔ ፀረ ሕዝብነቱን በዕብሪት ሲያሳይ ዓመታት አልፈዋል::

ወያኔ ላለፉት ሀያ ዓመታት የፈጸመው ፀረ ኢትዮጵያ ድርጊት ሁሉ በቂ ትምህርት ነውና ዛሬ ወደኋላ ተመልሶ ስለ ወያኔ ብኽታን ማስተናገድ ሀገርን ይጎዳል:: ከተራ ቂልነት አልፎ ወደ ወንጀል ደረጃ የሚፈርጅ ነው:: ከደረሰብን መከራና ስቃይ መማር አለብን::

ምከረው ምከረው እንቢ ሲል መከራ ይምከረው የሚባልብን መሆን የለብንም:: ታሪክ ቅርስ ነው፤ በደም የተገበየ ተመክሮ ደግሞ ወርቅ ቅርስ ነው:: ስህተትንም ፀጋንም ቁልጭ አድረጎ ያሳያልና:: ስህተትን እንዳንደግም ቀይ መብራት ያሳየናልናም ነው:: ከትግል ተመክሮ መማር እንታገል ለሚሉ አስፈላጊና ግዴታም ነው። ታሪኩን የረሳ ስህተቱን ይደግማል ነውና::

የወያኔ አገዛዝ አፈናና ጭፍጨፋ መሰረቱና መንቀሳቀሻው ነው:: ሌላ መንገድና ዘዴን አያውቅም፤ አይፈልግም:: ያለፈው ቢቀር እንኳን ዛሬ የሙስሊም ኢትዮጵያውያንን ፍትሐዊ ተቃውሞ በቀና ምላሽ ከመስጠት ፈንታ ሊያፍን እየጣረ ነው:: አመጽ ግዳጅ ነው በሚል ርዕስ መያዝ የተገደድነውም ይህን የህዝብ ተቃውሞ ሁሉም ዜጋ ሊደግፈው ሊያጅበው ይገባልየሚለውን ለማሳሰብ ነው::

# ነጻ ሀሳብ

በየካቲት 66 ሙስሊም ዜጎች መብታችን ይከበር ብለው ሲሰለፉ ክርስቲያን ወገናቸው አብሮ ተሰልፏል:: ዛሬም ይህ እውን መሆን ያለበት መከሰት ያለበት ነው:: የዜግነትን ግዳጅ መዘንጋቱ ሀገርን ይጎዳል:: ግዳጅን መወጣት በሚመለከት ተልካሻ ምክንያቶችን እየደረደሩ ከትግል መራቁም የሚደገፍ ሳይሆን የሚወገዝ ነው::

ፍርሀትን ማሸነፍ ደግሞ ለሀገር ስርየት ወሳኝ ነው:: የዜጎች ሕይወት ዋና ባለቤት ደግሞ ኢትዮጵያ ናት:: ለሀገር መሞት ሕይወት፤ ዳግም ትንሳዔ ስርየት መባሉ ተገቢ ነው:: ለሀገር ከመሞት በላይ ክብር የለምና:: ለዚህም ነው ነጋ ጠባ ለወያኔ መሰሪ ፕሮፓጋንዳ ወይም ሰበካ ሰለባ መሆን የሌሉብን:: መለስ ዜናዊ ከሞተ ቡኋላ በፖለቲካው መድረክ በተወሰነ ደረጃ ለውጥ የሚከሰት መሆኑም ግልጽ ቢሆንም (ለምሳሌ ወያኔ ውስጥ ሽኩቻ) ስርአቱ የተለወጠና በቀና መንገድ ሊጓዝ የወሰነ አድርጎ ማቅረቡ ደግሞ ቅዠት መሆኑ ግልጽ ነው::

በ[ህየፑር] አድምጠነዋል:: ለወያኔ ጊዜ ይሰጠው ብለው ፀረ ወያኔውን ትግል ያወገዙ ለፀረ ሕዝቡ አገዛዝ መደላድል አስተዋጽኦ አድርገዋል:: አዲስ ጠቅላይ ሚኒስቴር የተባለው የሰናፍጭ ቅንጣትም ያህል ሥልጣን የለውም:: ወዝግቡ በበረከት ሰምኦን አዜብ ጎላ ቡድንና በስብሀት ነጋ ቡድን መካከል ነው:: ይህ ሁሉ አዲስ ጠቅላይ ሚኒስቴር ተብዬውን አይመለከተውም:: አዲስ ጠቅላይ ሚኒስቴር ተብዬውም በሲዳማ ህዝብ ፍጅት የተካፈለ ወንጀለኛ ነው:: ንጹህ ዜጋ አይደለም::

ገገር ነን ባዮች በመሻኮታቸው ሚዛን አልባውን ግለሰብ ጠቅላይ ሚኒስቴር ብለው ሊያስቀጥሉ መወሰናቸውን በአልባሌ መንገድ በማንበብ ገለባውን ግለሰብ ለሲዳማ ፍጅት ተጠያቂ ሆኖ ሳለ በጥፋት የሚከሰስ አይደለም ብለው ሊከረከሩ የሞከሩ በባዕድ ሀገር የሚኖሩ ምሁር ተብዬዎችንም ታዝበናል:: ከታሪክ አለመማር ደግሞ ለግለሰቡ ጊዜ እንስጠው የሚለው አሳፋሪ አቅዋም ነው::

ለዚህ ኢምንት ግለሰብ ጊዜ እንስጠው በሚል ለሚገቱ የተነሱ ደግሞ ከባድ ስህተት እየፈጸሙ ናቸው::የመለስን ፀረ ሕዝብ አገዛዝ ለመቀጠል ዛሬ ለውጥ መጣ በሚል፣ ለምሳሌ የስደቱ ሲኖዶስ ከወያኔ ሲኖዶስ ጋር መስመር መስማማት አለበት ብለው የሚገፉትም በሀገር ትግል ላይ በደል እየፈጸሙ ናቸው:: የተወሰነው የሕብረተሰብ ክፍል በተቃውሞ ሲነሳ ይህን አለመደገፍም ሀገርን የሚጎዳ ነው:: ይህን በተመለከተ ተመክሮ አለንና ከዚህም መማር ይገባናል::

ሁናቴው ባልተለወጠበት አቅዋምን መለወጥና መሸመድመድ የሚጠቅም አይሆንም:: ዛሬ ሕዝብ የጠላው ዘረኛ የወያኔ ቁንጮ ስለሞተ ወያኔ ጨምቶና ሀገር ወዳድ ሆኖ የሚከሰት አይደለም:: በወያኔ ውስጥ ለኢትዮጵያ የሚበጅ ቀና ራዕይ ያለው ከቶም የለም:: የቀድሞ ወያኔዎችና ተቃዋሚ ነን ያሉትም የቁርጥ ቀን ሲመጣ ሽንፍላ ቢታጠብ አይጠራም ሆነው ተገኝተዋል::

ካለፈው ለመማር ከተነሳን በሁሉም መስክ በቀናም ሆነ በስህተት ብዙ ትምህርትን ገብይተናል:: ጠላትን አምርሮ መታገል ወሳኝ መሆኑንም ተረድተናል:: ቆራጥና ጽኑ ትግል መካሄድ ባለበት ወቅት ከንድን በሰበብ ባስባቡ የሚያዝሉትን መታገልና ማሸነፍ አለብን:: የራስን ጉድፍ ማስወገዱ መቅደም አለበት:: ተቃዋሚ ድርጅቶችን የጎዳው ወያኔ ብቻ ሳይሆን በየድርጅቶቹ ያሉት የነበሩት ወላዋይና ተሸናፊዎች ናቸው:: እንኟ ፈጣሪዎች::

ህብረት ግንባርን በተመለከተ ያለን ተመክሮ ሰፊ ነው:: ይህ ውጤት አስገኝቷል ይህ ግን አልጠቀመም በሚል ትምህርት ቀስመናል:: በዚህ መጠቀም መጣሩ ተገቢ ነው፡ ላለፉት 20 ዓመታት ወያኔ ማንነቱን በከፋ መንገድ ለሕዝብ አሳይቷል:: ዕርቅ ወሰላም በሚል ለተደረገው ሙከራ ሁሉ ወያኔ መልሱ በአቋራጭ ስልጣን አትካፈሉም ወግዱ የሚል ነበር:: ዛሬም ነውም:: ወያኔ በምንም ዓይነትና ሁኔታ ሰላምና ዕርቅን የሚፈልግ አለመሆኑን አሳይቷል::

በሰላምና በድርድር ስልጣን ሊለቅ ቀርቶ ሊካፈልም ዝግጁ አልነበረም/አይደለም:: ለዚህም ነው ዛሬ አዲስ የይስሙላ ጠቅላይ ሚኒስቴር ስለተሰየመ ከወያኔ ጋር እርቅ ወሰላም ፍለጋ መነሳቱ ራስን ማሞኘት ነው:: ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ነው:: ጠቅላይ ሚኒስቴር ተብዬውም ሆነ ጌታው በረከት ሰምዖን የመለስ መንትዬዎች ናቸውና ልዩ አቅዋም ወይም ሰብዕና የላቸውም:: ነውናም የወያኔን ዘረኛ አገዛዝን ማስወገድ በተመለከተ በሀይል ከመደምሰስ ሌላ አማራጭ መውሰድ ወይም መስበክ ከቶም አይቻልም፤ አያዋጣም:: ማመጽ ግዴታ ነው፤ ብሔራዊ ግዳጅ ነው:: ከአመጽ ውጪ መፍትሔ የለም:: አለ የሚሉ የተወናበዱ ወይም በወያኔ የተገዙ አወናባጆች ናቸው::

በወያኔ አገዘዝ ላይ እናምጽ!

የወያኔ አገዛዝን በአመጽ እናወድም!

## ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች…

ከ ፩ ገፅ  የዞረ ታዲያ የፃነነትና የፍትህ ትግል አልጋ ባልጋ አይሆንምና ታሥረውበታል፤ ተቀጥቅጠውበታል፤ ተሰደውበታል ብሎም ክቡር ሕይወትን በአርሲ፤ በወሎ፤ በአዲስ አበባ አሥገብረቻቸዋል። ክቡር ለሰማእታት ይሁንና ስልታቸውን በጥበብ እየቀያየሩ አስደናቂና አኩሪ ትግላቸው ክርስቲያኑ ወገንም ወደጎናቸው መሳቡ በአለፈው ቃሊቲ የእሥር መንደር ጎልቶና ደምቆ ታይቷል።
ጥራት ያለውና ቆራጥነትን የተላበሰ አመራር ጽኑ ሕብረተሰብ ይፈጥራልና የሙስሊሙ የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባሎች ጽናታቸው በሕዝብ ልብ ውስጥ ታላቅ የፍቅር ሥፍራ ተችሮአቸዋል። ባለፈው ሁለት ሳምንት ሙስሊሙ ሕብረተሰብ የትግል ቀጠሮውን ወደቃሊቲ በማዞር በሙቶ ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በመትመም በአለም የመጀመሪያ ሊባል የሚችል የእሥረኛ ጠያቂ ትዕይንት በቃሊቲ እሥር ቤት ውሥጥና ውጪ አሳይተዋል።



ፅናታቸው የሚሊዮን ኢትዮጵያውያንን ፍቅር አግኝቷልና ክርስቲያኑ ሕብረተሰብም እጅበዋቸው በፀሀይ ለተቃጠሉ እሥረኛ ጠያቂ ሕዝብ ውሀና የሚበላ ሲያድሏቸው ታይቷል። በህዳር ሃያአንድም ቀጠሮ በልደታ ፍርድ ቤት የተያዘላቸውን የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት እሥረኞችን ለመዘየርና የእንበለ ፍርድን ለመከታተል በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ወደ ልደታ ተጉዘው ነበር። ሰላማዊ ትግል የማይገባቸው ወያኔዎች ሰላማዊ ዜጎች የለበሱትን የእስልምና መለያ ልብሶችን እየገፈፉ ኀህይማኖታቸውን ጭምር ሲሰድቡ ተደምጧል። ትግላቸው ግን ቀጥሏል።

ከዚህ ትግል ትምህርት የቀሰሙና ፍራቻን ያሸነፉ ሌሎች ብሶት ያንገሸገሻቸው መኖርያቸው በወያኔ የፈራረሰባቸው ኢትዮጵያውያን በዚያው ሰሞን በእሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ወደማዘጋጃ ቤት በሰልፍ ወጥተው ተቃውሞአቸውን ሲያሰሙ ውለዋል። እኛም የኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች ምንጊዜም ከሕዝባችን ጎን እንዳለን እየገለፅን የተቀረውም ብሶተኛ ወገን አብሮ ካልተሰለፈ እውነተኛ ለውጥ ሊመጣ አይችልምና መብቴን፤ ሀገሬን፤ ነፃነቴን፤ ሃይማኖቴን ያልከ ኢትዮጵያዊ በሙሉ ይህ ወርቃማ እድል እንዳያመልጥህ ስንል መልክታችንን እናስተላልፋለን። የሰላማዊ ተቃዋሚ ድርጅቶች ነን የምትሉ በሀገር ቤት ያላችሁ ከወጣቶቹ ትምህርት  ቀሥሙችሁ የሰላም ትግላችሁን ሕብረተሰቡን በማስተባበር ፊንታ ሰልፍ እንዳንወጣ ፈደራል ፈቃድ ከለከለን ሀጎሥ አባረረን የሚል ሠንካላ ሰበብ ተዉት እንላለን። አለበለዚያ አርፋችሁ ተቀመጡ እንላለን። አሊያም የእናንተ ሰላማዊ ትግል ሳይሆን ሰላማዊ ኑሮ ተብሎ እንዳይጠራ!!!

(ታጠቅ ከዱሲ)

## የወያኔ ባለስልጣናት መተራመሳቸውን እንድቀጠሉ ነው

ከ ገፅ ፫ የዞረ

በዘመድ አዝማድ የተተበተበ ኪራይ ሰብሳቢነት ያሳዩ… የተሰጣቸውን ስራ በአግባቡ የማይወጡ…በመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ለውጥ ካላሳዩ ከስልጣናቸው ከመነሳታቸውም በተጨማሪ እንደ አስፈላጊነቱ ሊከሰሱ እንደሚችል በስብሰባው ላይ መግለጹንም ምንጮቹ ገልጸዋል:: ለ21 ዓመታት በህዝብ ጫንቃ ላይ ሲያናጥሩ የኖሩትና በህዝብ እና በሀገር ላይ ደባ ሲፈጽሙ የነበሩትን እነዚሁ የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት ከተጠያቂነት ለማዳን ሲባል አዲስ ዘመቻ የጀመሩ ሲሆን እግረ መንገዳቸውን የህዝብ ድጋፍ ለማሰባሰብ እንዲረዳቸው ያደረጉት መሆኑንም ምንጮቹ አክለው ገልጸዋል::

የህዝብ ድጋፍ ለማግኘት ከተፈለገ ጥፋት ያጠፋው ባለስልጣን ጥፋቱ ለህዝብ ይፋ ተደርጎ ቅጣት ሲጣልበት መሆኑን ሲሞግቱ የሰነበቱት አፍለኛ ባለስልጣናት በአሁኑ ሰዓት የሕዝቡ ድጋፍ ካልታከለ በስተቀር ድርጅቱ ከፍተኛ አደጋ ላይ ሊወደቅ እንደሚችል መናገራቸውን ምንጮቹ ገልጸዋል:: ቀድሞ የነበረው የርስ በርስ ሽኩቻና ንትርክ እልባት ሳያገኝ በእንጥልጥል ላይ እንዳለ ሆኖ አሁን ደግሞ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ ስልጣንን አለአግባብ መጠቀም… በሚሉ ጉዳዮች ላይ ውይይት ሲያደርጉ የነበረ ቢሆንም ነባሮቹ የወያኔ ባለስልጣናት እስከዛሬ የፈጸሙትን በደል የሚያጋልጥባቸው በመሆኑ ሊሰራጭ የነበረው ሙሉ ፕሮግራም ተቋርጦ እንዲቀርብ መደረጉንና ይህንኑ ተከትሎ ብዙ ወጣት ባለስልጣናት ከፋኛ መቆጣታቸውን ምንጮች አረጋግጠዋል::

በሌላ ዜና ህወሀት ከተመሰረተና ስልጣን ካይ ከወጣ ጀምሮ እስከዛሬ ያልተደረገ ህዝባዊ ስብሰባ በትግራይ ሁሉም ከተሞች በግዴታና በድለላ መደረጉን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋለጠ:: በመቀሌ ከተማ ሰማዕታት አዳራሽ ተብሎ በሚጠራው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ የህወሀት ከፍተኛ አመራሮች ብቻ ሲመከሩ የሰነበተ ሲሆን ይህንኑ ሚስጢራዊ ስብሰባ ተግባራዊ ለማድረግ በመላ የትግራይ ክልል ከተሞች ህዝቡን እያስገደዱ፣ እያስፈራሩና በገንዘብ እየደለሉ ህዝባዊ ስብሰባ ሲያደርጉ መሰንበታቸው ታውቋል::

በመላ ትግራይ ከገጠር እስከ ከተማ ነዋሪ የሆኑ እድሜያቸው ከ፲፫ ዓመት እስከ ፳፫ ዓመት ያሉትን ዜጎች በግዴታና የውሎ አበል በመክፈል ስብሰባ የተደረገ ሲሆን ዋነኛው አላማ የህወሀትን ከዚህ ቀደም ከነበረው በላይ በሀገሪቱ የበላይ ሆኖ እንዲቀጥል ለማድረግ እንደሆነም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ያስረዳል:: ስብሰባውን በተለያዩ ቦታዎች ተከፋፍለው ሲመሩት የነበሩት ነባር የበረሀ አመጣሽ ሽማግሌ የህወሀት ባለስልጣናት ሲሆኑ እነሱም ሴቶቹን፣ ወንዶቹን፣ ወጣቶቹን እና ባለሀብቶቹን በመለያየት እና በመከፋፈል የትግራይ ህዝብ ከተቀረው የሀገሪቱ ወንድሙ ጋር በሰላምና በፍቅር እንዳይኖር ቅስቀሳ ሲያደርጉ መሰንበታቸው ታውቋል::

ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጊዚያት የትግራይን ህዝብ ከተቀረው ወገኑ ጋር ለመጋጨት ሞክረው ያልተሳካላቸው የወያኔ እድሜ ጠገብ ሽማግሌ ባለስልጣናት ጡረታ በመውጫቸው ላይ አሁን እንደ አዲስ ህዝብን ሊያጋጩ ቅስቀሳ መጀመራቸውን ህዝቡ መቃወሙንም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አስረድቷል:: የህዝብ ድጋፍ ያጡት እና ዙሪያው ገደል የሆነባቸው የወያኔ በተለይ የህወሀት ነባር ባለስልጣናት እስከዛሬ ለሰሩት ግፍና ለፈጸሙት በደል ንስሀ ገብተው ህዝቡን ይቅርታ ከመጠየቅ ይልቅ እርስ በርስ እንዲከፋፈል እና ችግር ውስጥ እንዲዘፈቅ ለማድረግ በትግራይ ውስጥ እየተዘዋወሩ ቅስቀሳ ሲያደርጉ መሰንበታቸው አሳፋሪና አሳዛኝ ነው ሲል የተግራይ ህዝብ በብስጭት ሲናገር ተደምጧል::

## መምህር በላይነህ ገ/ማርያም

በሞቱ ጠላቶቹን ድል የነሳ የኢሕአፓ ኮከብ
(ምንጭ፤ ጎሕ መጽሔት ሚያዝያና ግንቦት ፩፱፻፺፫ ዓ.ም)
ከ ገፅ ፭ የዞረ

ጎን ለጎንም የኩብት ርባታ ያካሄድ ነበር ። በአካባቢዉ ከነበሩት አርሶ አደሮችና የቀን ሠራተኞች ጋር ለመዋሃድና በተግባር ለማገዝ እንዲመቸዉ በማሰብ ነበር ይህንኑ ሥፍራ የመረጠዉ።

የቀኑን የማስተማር ሥራዉን እንደጨረሰ ከቃሊቲ ወደ ሶራቲ በአሮጌይቱ ሬኖ መኪናዉ ሆኖ ወይም በእግሩ ዋልካዉን አቋርጦ ይጓዛል ።ሰላሳ የሚሆኑ የአካባቢዉን አርሶ አደሮችና የቀን ሠራተኞች በራሱ ወጪ ጥቁር ሰሌዳ ፤ ጠመኔና ማሾ ገዝቶ ማታ ማታ በማስተማር ከማይምነት አላቅቋቸዋል ።

መምህር በላይነህ ገ/ማርያም ራሱን ለትግሉ አሳልፎ የሰጠ ጓድ ነበር ።በኢሕአፓ አባልነት መንቀሳቀስ ከጀመረ በኋላ መኖሪያ ቤቱንም እንደ ሕይወቱ ለድርጅቱ እንቅስቃሴ መገልገያ እንዲሆን አሳልፎ ሰጥቷል ።በቤቱ ዉስጥ ድርጅቱ ለፕሮፓጋንዳና ለቅስቀሳ የሚጠቀምባቸዉ ጽሁፎች ይባዙ ነበር ። የዲሞክራሲያና የላባደር ዕትሞችም እዚያዉ እየተባዙ ወደተለያዩ ሥፍራዎች እንዲሰራጩ ተደርገዋል ።

***   ***   ***   ***

ሻለቃ መንግሥቱ ኃ/ማርያምን ለማስወገድ የተካፈለበት ኦፐሬሽን ያለመሳካቱን የተረዳዉ በማግሥቱ ነበር ።ድርጅታቸዉን ከአደጋ ለመታደግ ለቆረጡት መምህር በላይነህን ለመሰሉ የኢሕአፓ ጀግኖች ጊዜዉ ባልተሳካ ዕቅድ ተስፋ ቆርጠዉ የሚቀመጡበት አልነበረም ። ትግል ባለበት ሁሉ ጀግኖች በእሳት የሚፈተኑበት አጋጣሚ በርካታ ነበርና ለሚቀጥለዉ ግዳጅ ለመወርወር  በልበ ሙሉነት ተዘጋጀ። ቀጣዩ ተልዕኮ ደግሞ ሩቅ አልነበረም ።

(በሚቀጥለዉ ዕትም ይጠብቁን )




አሸባሪ በሉን
እሰሩን ቀጥቅጡን
ግረፉን እንገረፋለን
አሳዱን ግድየለም እንሰደዳለን
እናንተም ግደሉን
እኛም እንሞታለን
እናንተ ግን ትቢያ !
ኢንሻ አላህ
እኛ እንነሳለን!!

(ከሙደሲር ኡስማን)




**ከንግዲህስ ይብቃ በቁም መሞት ይቅር!**

**እንደእሳት የፈሩት ያብብ የሐገር ፍቅር!**

**ኢትዮጵያዊነት ማእበል ይሁንና!**

**የጎበዝ አለቃ ይውለድ ብዙ ጀግና!**

